# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**የከቲተ 19 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**ወያኔ እጅግ አደገኛ መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ በህዝቡ መሀል መንዛት ጀመረ፤**

**ከባድ የጦር መሳሪያ በአዲስ አበባ በድብቅ ማስገባቱ ተጋለጠ፤**

**ለፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ መኮንኖች የተሰጠው የማዕረግ እድገት ቅሬታ አስነሳ፤**

ወያኔ በተለያዩ አቅጣጫዎች ከህዝቡና ከነጋዴው በኩል በደረሰበት ከፍተኛ ተቃውሞና ኩርፊያ አጣብቂኝ ውስጥ በመውደቁ የተነሳ እጅግ ግራ አጋቢ እና አደገኛ እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑ ታወቀ::

ወያኔ በፈጠረው ችግር ምክንያት ህዝቡ በኑሮ ቀውስ ውስጥ ወድቆ ከመገኘቱም በተጨማሪ ከጎረቤት ሀገር ጅቡቲ ጀምሮ እስከ ሰሜን አፍሪካ ድረስ የህዝቡ ተቃውሞ አይሎ መሪዎችን እየፈነገለ ባለበት በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የኑሮ ውድነቱ በህዝቡ ላይ ጫና በመፍጠሩ ተመሳሳይ እርምጃ ሊወስድ ይችላል በሚል ስጋት ከፍተኛ ገንዘብ በመመደብ የደህንነት ሰራተኞችን በየመንደሩ አሰማርቶ እንደሚገኝ ታውቆዋል::

በተለያዩ ሀገራት ህዝብ ብሶቱን በየአደባባዩ ከመግለፁም ባሻገር መሪዎቹን እየመነገለ በማባረሩ ስጋት እና ፍርሀት የገባው ዘረኛው እና ሰው በላው የወያኔ አምባገነን ቡድን በየሰፈሩ እና በየመንደሩ የህዝቡን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ሲል እጅግ ቁጥራቸው የበዛ ሰላዮችን እየበተነ መሆኑ ተጋልጦዋል::

ወያኔ ከዛሬ 20 ዓመት በፊት ከደደቢት በረሀ መጥቶ የአራት ኪሎ ቤተመንግስትን እንደያዘ ህዝቡን ለመቆጣጠር እንዲያመቸው በብሔር እና በተለያዩ ሀይማኖቶች ሲከፋፍል እና ሲያጋጭ አንደነበረው ግዜ ሁሉ ሰሞኑንም በተመሳሳይ ሁኔታ ይህንኑ ሴራውን ተግባራዊ ለማድረግ እየሰራ መሆኑ ታውቆዋል::

ለራሱ ስልጣን ያሰጋው ወያኔ ለከፋፍለህ ግዛ ስልቱ እንዲያመቸው ተፋቅሮና ተሳስቦ የኖረውን ህዝብ ለማጋጨት እና የእፎይታ ግዜ ለማግኘት ሲል አዲስ ስልት ቀይሶ ሰላይና ጆሮ ጠቢዎቹን በህዝቡ ውስጥ አሰማርቶ እየሰራ መሆኑን ከደህንነት ቢሮ ሾልኮ የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል።

በጥቅማጥቅም ሸንግሎ አባል ያደረጋቸው የሴቶች እና የወጣቶች ፎረም አባሎችን ጭምር ከደህንነቶቹ እኩል በህዝቡ መሀል በትኖ የስለላ ስራ እንዲሰሩ ከማድረጉም በተጨማሪ በህዝቡ መሀል ክፍተት እንዲፈጠር እና በሀገሪቱ ውስጥ ሰላም ጨርሶ እንዳይኖር አደገኛ የፕሮፓጋንዳ መርዝ እየበተነ መሆኑን የደህንነት ምንጮች አጋልጠዋል።

በሁለት መልኩ ተከፋፍለው እየሰሩ ያሉት እነዚሁ የወያኔ ቡችላ ሰላዮች አንደኛው በደህንነቱ የበላይ ሹም ጌታቸው አሰፋ የሚመራ ሲሆን ሌላው ደግሞ በበረከት ስምዖን እንደሆነ የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ በበረከት የበላይነት የሚመራው የፎረም አባሎች ቡድን በየሰፈሩ እየዞሩ አንዱን ብሔር ከሌላው ለማለያየት እየሰሩ መሆኑ ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በዚህም መሰረት አማራውን ነፍጠኛ ነው ሲያስገብረን የኖረ ነው እያሉህ ነው ኦሮሞውን ደግሞ እራሱን ችሎ የማይንቀሳቀስ ተለጣፊ እየተባልክ ነው የደቡብ ተወላጅ የሆኑትን አናሳ ናችሁ እያለ እያሏችሁ ነው የትግራይ ተወላጆችን ደግሞ ርሀብተኛ እና ለማኝ ነህ ሰርቶ የማይበላ ይሉሀል በሚል ዘረኛ እና በታኝ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ሕዝቡን እርስ በርስ ለማጋጨት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ሲሆን ይህም ወያኔ ህዝባዊ ተቃውሞው በራሱ ላይ እንዳይነሳበት የፈጠረው ዘዴ መሆኑን እነዚሁ የደህንነት ምንጮች አጋልጠዋል።

ዛሬ የኑሮ ውድነቱ ህዝቡ መሸከም ከሚችለው በላይ ሆኖበት የአምላኩን ቸርነት እየለመነ ባለበት ሰዓት እና ችግሩን እርስ በርስ ተደጋግፎ እንዳይወጣ ለማድረግ ሲሉ የወያኔ የደህንነት ሰዎች በምስጢር በህዝቡ ውስጥ ከፍተኛ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እየነዙ መገኘታቸው ወያኔ ለስልጣኑ እንጂ ለሀገር እና ለህዝብ የማያስብ መሆኑን ያሳያል ያሉት ምንጮቹ ተወደደም ተጠላ መለስ ዜናዊ እንደ ሊቢያው መሪ ሞአመድ ጋዳፊ በአደባባይ መዋረዱ አይቀሬ ነው ሲሉ እነዚሁ የደህንነት ምንጮች ገልፀዋል።

በአሁኑ ሰዓት የተጀመረው እጅግ አሳሳቢ እና አደገኛ በመርዝ የተለወሰ ፕሮፓጋንዳ ህዝቡ አስቀድሞ እንዲያውቀ ተደርጎ የወያኔን ሴራ ማምከን መቻል አለበት ያሉት ምንጮቹ በተለይ ጥቂቶቹ የደህንነት ባለስልጣናት በህዝቡ መሀል እየሰሩ ያሉት ሸፍጥ በጭሩ ካልተጋለጠ አደገኛ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸው ጨምረው አጋልጠዋል።

በተያያዘ ዜና ከፍተኛ ስልጣኖችን እና ቁልፍ ቦታዎችን በአንድ ወገን የበላይነት ስር እንዲገባ ያደረገው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ እጅግ በተጠናከረ መልኩ ቁልፍ ቦታዎች በህወሀት ሰዎች እንዲያዝ ማድረጉን አጋልጠዋል።

ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቁልፍ ቦታ እስከ ደህንነት መዋቅሩ...... ከፌዴራል ፖሊስ ልዩ ኃይል እስከ መከላከያው ድረስ ቁልፍ እና ወሳኝ የሆኑ ቦታዎችን ተቆጣጥረው ያሉት የህወሀት ሰዎች አሁንም የበለጠ ስልጣናቸውን እያጠናከሩና እየተቆጣጠሩ መሆኑ ታውቆዋል።

የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረውና በጡረታ የተሰናበው ፀጋዬ በርሔ የተባለው ግለሰብ ከቦታው ተነሳ ቢባልም ዛሬ ተመልሶ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ከፍተኛ አማካሪ በመሆን የተሾመ መሆኑ ታውቆዋል።

በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ውስጥ ሙሉ ስልጣን የተሰጠው የደህንነት መዋቅሩ ሙሉ ለሙሉ በህወሀት የተያዘ ሲሆን በቅርቡ በምስጢር እየተሰራ ያለውን አፍራሽ እና መርዘኛ ሴራ እየተገበሩ የሚገኙትም እነዚሁ አረመኔ ግለሰቦች መሆናቸው ታውቆዋል።

በሌላ ዜና በጎረቤት ሀገር ጅቡቲ ውስጥ የመለስ ሸሪክ የሆነው ኡመር ጉሌህ ከስልጣኑ ይውረድ ብሎ ህዝቡ ተቃውሞ በማቅረቡ የተደናገጠው ወያኔ ጦሩን ወደ ድንበር ማስጠጋቱ ታውቋል። ከዚህ በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ባሉ ከተሞች ውስጥ በሚገኙ ወታደራዊ ካምፖች የወታደር ቁጥር እየጨመረ መሆኑ ሲገለፅ አንድ ተወርዋሪ የከባድ መሳሪያ ምድብ ጦር በምስጢር በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መሸጎ መቀመጡን የመከላከያ ምንጮች አጋልጠዋል።

በምስራቅ እዝ ዋና አዛዥ ሜ/ጄ/ል አብርሀ ወ/ማርያም በበላይነት የሚመራው ወደ ጅቡቲ ድንበር የዘመተው የወያኔ ጦር በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በአካባቢው ጥብቅ ቁጥጥር ከማድረጉም ባሻገር ከጅቡቲ በሚገቡና በሚወጡ ዜጎች ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል ፍተሻ እንደሚያደርግና ለሰዓታትም ለጥያቄ በሚል በቁም እስር ላይ እንደሚያውላቸው ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ዙሪያውን በፍርሀት ተወጥሮ ያለው የወያኔ ቡድን በጅቡቲ ድንበር ላይ ጦሩን ከማስፈሩም በተጨማሪ በየጦር ክፍሎች ውስጥ ከመቼውም ግዜ በላይ የህወሀት መኮንኖቸ ቁልፍ ቁልፍ ስልጣን እንዲይዙ እያደረገ መሆኑን ያጋለጡት የመከላከያ ምንጮች በቅርቡም የሰራዊቱ አባሎች አዲስ ዝውውር እንደሚደረግላቸው ምንጮቹ ገልፀዋል።

የወያኔ ቡድን ሰራዊቱን በአራት እዝ ከፋፍሎ ያሰማራ ሲሆን ከቅርብ ግዜ ወዲህ ሕዝባዊ አመፅ በተከሄደባቸው የሰሜን አፍሪካና የመከከለኛው ምስራቅ ሀገራት ውስጥ ሰራዊቱ ከህዝቡ ጋር ወግኖ አምባገነን መሪዎቹን እየፈነገለ መሆኑን የተረዱት የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናትና ጄኔራሎች ጦሩን ከነበረበት ክፍል ወደሌላ በግለሰብ ደረጃ በማዘዋወር እየበታተኑት መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

በምዕራብ ዕዝ የነበሩት የጦር ክፍሎች እና ወታደሮች ወደ ሰሜን እንዲሁም የማዕከላዊ ነባር የሰራዊቱ አባሎች ወደ ምስራቅ እዝ እየፐወዙ ያሉት የወያኔ ጄኔራሎች በሰራዊቱ ቅሬታ የቀረበበት የጦር ጄኔራልም ከቦታው እንዲነሳ መደረጉንም ምንጮቹ አስረድተዋል።

በምዕራብ እዝ ውስጥ ዝውውሩ ተግባራዊ መደረግ የተጀመረ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በጦሩ ውስጥ ከፍተኛ ትርምስ እየተፈጠረ በመሆኑ ስጋት ያደረባቸው እነ ጄ/ል ሳሞራ የኑስ የእዙን አዛዥ ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ መኮንኖችንም እየበተኑ እንደሆነ አብራርተዋል።

ለብዙ ዓመታት የምዕራብ ዕዝ ዋና አዘዥ ሆኖ ሲያገለግል የቆየው ሜ/ጄ/ል ስዩም ሀጎስ የተባለው ግለሰብ በሰራዊቱ በቀረበበት ተቃውሞ ምክንያት ከቦታው እንዲነሳ የተደረገ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት መከላከያ ዋና ቢሮ ውስጥ በአንድ መምሪያ እንዲቀመጥ መደረጉንም ታውቀዋል።

የእዙ አዛዥ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት በሱማሊያ ዘመቻ ላይ ያለ በቂ ጥናት እና እቅድ በሺህዎች የሚቆጠሩ የጦሩ አባሎችን ያስጨረሰ በመሆኑ ሊጠየቅ ይገባል በማለት የእዙ አባሎች ጥያቄ በማቅረባቸው ምክንያት ከቦታው የተነሳ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮቹ ግለሰቡ በህግ መጠየቅ እና በሞቱት ዜጎች ሊወነጀል ሲገባ ይባስ ብለው ወደ መከላከያ መምሪያ እንዲዘወር ተደርጎ መቀመጡ እጅግ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲሉም ገልፀዋል፡፡

የአንድ ወገን የበላይነት የሰፈነበት መሆኑ የተረጋገጠው የወያኔ መከላከያ በጦሩ ጥያቄ የተነሳው ምትክ ለይምሰል የብሔር ተዋፅኦ አለ ለማሰኘት ሲባል ብቻ ምክትል አዛዥ ሆኖ በብ/ጄ/ል ማዕረግ ሲሰራ የነበረውን  አንድ ማዕረግ ከፍ ተደርጎ የሜ/ጄ/ልነት ማዕረግ ተሰጥቶት ቦታውን እንዲይዝ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

ሜ/ጄ/ል ብርሀኑ ዱላ የተባለው ይሄው የወያኔ ተላላኪ ግለሰብ ለግዜው የጦሩን ጥያቄ ለማርገብ ሲባል ቦታውን እንዲረከብ የተደረገ ቢሆንም ከስሩ የተቀመጠው ግን የህወሀት ታጋይ የነበረ ግለሰብ መሆኑን ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

በመጨረሻም  ወያኔ ለቀድሞ መኮንኖች ማዕረግ መስጠት ማለት በመቃብሬ ላይ አፈር ማልበስ ነው ሲል ሲፎክር እና ሲያቅራራ እንዳልነበር  ድንገት በተለያዩ ሀገራት የፖለቲካ ቀውስ በመፈጠሩ ባደረበት ውስጣዊ ፍራቻ ምክንያት ሳይወድ በግድ ድንገተኛ የማዕረግ እድገት መስጠቱ ታወቀ፡፡

በእውቀት እና በችሎታቸው የሚፈራቸው የቀድሞ ከፍተኛ የፖሊስ መኮንኖች ለብዙ ዓመታት የማዕረግ እድገት ተከልክለው የቆዩ  ቢሆንም ዛሬ በጎረቤት  ሀገር ሳይቀር በተፈጠረ ተቃውሞ የደነገጠው ወያኔ ችግሩን ይቀርፉልኛል በሚል  ለከፍተኛ መኮንኖች የማዕረግ እድገት መስጠቱ ታውቆዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ከ10 ዓመት በላይ በሻለቃነት ሲታሹ የቆዩት የቀድሞ መኮንኖች የኮሎኔልነት ማእረግ እንደተሰጣቸው ታውቆዋል፡፡

ከዚህም ጎን ለጎን የትምህርት ደረጃንና ብቃትን መመዘኛ ያላደረገ የማዕረግ እድገት ከበረሀ ለመጡ የወያኔ አባላት መሰጠቱ ታውቋል፡፡ ይህም የተደረገው እነዚህ የወያኔ አባላት በወያኔ ላይ ችግር ቢመጣ ራሳቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ ከሚል ግምት ነው፡፡

ምንም እንኳዋን ከዓመታት ቆይታ በሁዋላ ለነባር መኮንኖቹ የማዕረግ እድገቱ የተሰጠ ቢሆንም በአሰጣጡ ሂደት ደስተኛ እንዳልሆኑ በተለያዩ መልኮች በግለፅ  ተቃውሞዋቸውን እየገለፁ መሆናቸው ታውቋል፡፡